# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

## ለሰፊው ሕዝብ

(ወዛደር፤ ገበሬ፤ ነጋዴ፤ ወታደር፤ ምሁር)

መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

እሁድ ግንቦት 9 ቀን 1990


### አዲሱ ምእራፍ ነብሩን ትግል እንዳያዘናጋው

ከተወሰኑ ወራት ጀምሮ በወያኔና ሻብያ መሪዎች መሃከል ቀስ በቀስ እየተከሰቱ የመጡት አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጦችና በዓለም መገናኛ ብዙሃን ሲዘገቡ ቆይተዋል፡፡ ጸረ ዴሞክራቱ የወያኔ አገዛዝ እነዚህን ግጭቶች ከዋናው ባለጉዳይ ከኢትዮጵያ ህዝብ ለመሸፈን ዝምታን ሲመርጥና አንዳድ ጊዜ ደግሞ እነዚህን ክስተቶች ለህዝብ ለማስታወቅ የሞከሩ ጋዜጠኞችን ሲያስርና ሲያንገላታ ቆየቷል፡፡ ዛሬ ይህ ሁሉ ቀርቶ የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት በሁለቱ የቀድሞ ቃልኪዳን ወዳጆች መሃከል ያለው ቅራኔ ሰፍቶ በመሄድ እስከደም መፋሰስ ያደረሰ መሆኑን ሃገራችንንና አካባቢውን ከፍተኛ ውዥንብር ውስጥ ሊጥል የሚችል ውጥረት መፍጠሩን አምኖ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለመላው ዓለም የፋ አድርጓል፡፡

ባለፉት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም በመንግሥት ደረጃ ባለቤት አጥቶ፣ ገዥዎቿ ለሻቢያ መሪዎች ጥቅምና እብሪት አጎብድደው፣ የሁልቱ ውገኖች ጥቅም በትጋዉ ቁጥር ለሻብያ እየትንበረከኩ፣ የራሳችን እያረረብን የሰው እያመሱ ብዙ አሳፋሪ፣ አስገራሚና እንግዳ ነገሮች ሲፈጸሙ ታዝበናል፡፡

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራውና መላ የኢትዮጵያ ህዝቦች እን ደወንድም የሚያዩት የትግራይ ሰፊ ህዝብ በሱ ስም በሱ በራሱ ላይና በሃገራችን ታሪክ፣ ክብርና ጥቅም ላይ ያሚፈጸማውን ወንጀል ባለው አቅምና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከፍተኛ መስዋእትነት እየከፈለ ፣ እየታሰረና እየተገረፈ፣ እየሞተና የቻለም እየተሰደደ የወያኔን አገዛዝ ሲቋቋመው ቆይቷል፡፡ የትግራይን ህዝብ ከጸረ ዴሞክራቲክ ገዥዎቹ ጋር ሆን ብለው በማምታታት ሊወነጅሉት ሲሞክሩ ከቆዩ አውቀው አላዋቂ ከሚመስሉ ወገኖች በስተቀር ይህንን ተጨባጭ ሃቅ ያልተገነዘበና ያልተረዳ ዜጋ ያለ አይመስለንም፡፡

ዛሬ በወያኔ በራሱ ውስጥ የኢትዮጵያን ጥቅም በማስቀደም ይቺ ታላቅ አገር ለሻብያ መሪዎች መንበርከኳ ይብቃ በማለት ትግል ሲያካሂዱ የቆዩ አንዳንድ መሪዎችና አባላት በዚህ ማንም ሊበግረው ባልቻለ የህዝብ ግፊት ታግዘው በዚህ ድርጅት ውስጥ የሚያጠራጥር የበላይነት የያዙበት ወቅት ትክስቷል ማለት ይቻላል ፡፡

በውያኔ ውስጥ የኢትዮጵያን ክብርና ጥቅም ቅድሚያ ሰጥተን እናስከብራለን የሚሉ ኃይሉች አይለው ለዚህ ዓላማ በይፋ መቆም መቻላቸው ለትግራይም ሆነ ለመላው የኢትዮጵያ

ህዝብ፣ እዲሁም ደግሞ ልዚህ ዓላማ በግንባር ቀደምትነት ሲታገሉ ለውያኔ ጥይት ራት ሆነው ለውድቁት ሰማእታትና አሁንም በወያኔ እስር ቤት በመሰቃየት ላይ ለሚገኙ ሃቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ አንድ ድል ነው እንላለን። ይህም ሆኖ ግን ይህ ክስተት ለኢትዮጵያችን ዴሞክራሲ፣ ለህዝቦቿ እኩልንትና አንድንት፣ ለማህበራዊ ፍትህና ለብልጽግና ለሚደረገው ትግል አዲስና ምናልባትም ውስብስብ የሆነ ምእራፍ ይከፍት እንደሆን እንጂ በቻውን የመፍትሄ ፈር የሚያሲዘን ክስተት አይደለም። የወያኔ ጸረ ዴሞክራቲክ አገዛዝ እስከቀጠለ ድረስ ፣ የወያኔ ምሪዎች እስካሁን የያዙት የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ የሚያስከትለው አደጋ በአገራችን ሰማይ ላይ እስካንዣበበ ድረስ "አዲስ ምእራፍ ነው፣ ካብሩ ትግል ይግፋ" ብለን ከመነሳሳት ሌላ የምንዝናናበትና ያምንዘናጋበት ምንም ምክንያት ያለም።

ከዚህም በመነሳት የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክብርና ጥቅም፣ የህዝቦቿ እኩልነትና አንድነት፣ የሃገችን ሰላምና ብልጽግና ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ ወገኖቻችን ሁሉ የሚከተሉትን ጥሪዎች ያቀርባል።

አንደኛ/ በህወሃት ውስጥ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም እናስከብራለን ለሚሉ ምሪዎችና አባላት። ይህ ትግል የናንተ ትግልና ራእይ በቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦች ትግልና ራእይ ነው። እኛ የሃገራችን ጥቅምና ደህንነት፣ ብልጽግናና ክብር ተደፈረ እያልን የምንገበገበው የግዛት አንድነቷ ጥያቄ ውስጥ ሲገባ፣ በዚች ሃብታምና ለምለም አገራችን ጥሮ ግሮ የሚኖረው ታታሪ ህዝባችን ከዓመት ዓመት በረሃብ እየተቀጣ ስናይ፣ ይህ ህዝባችን ሳይንስ ሊረሳቸው ቢቃጣው የሌለ ዘመን በሽታውች ሲረግፍ ስንመለከት፣ ይቺ አገራችን መላውን አፍሪካ በማካበስ ላይ ካለው የዴሞክራሲ ንፋስ ተነጥላና ተዋርዳ ስንሸማቀቅ፣ የሰው ልጅ መብት አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ እየተረገጠበት ድፍን ዓለም እንደጉድ ሲመለከታት፣ የሰው ልጅ መብት አስከባሪ ድርጅቶች ነጋ ጠባ በስመጥፋነት ሲጠቁሟት፣ ዜጎች በጠራራ ጸሃይ አውራ መንገድ ላይ እየተረሸኑ የሰማእቶቻችን ደምና የቀሪ ዘመድ እምባ የፍትህ ያለህ እያለ ሲጮህ ስንሰማ፣ በታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው ሁኔታ ኢፍታሃዊነት ነግሶ ጨቅላ ልጆቿ ከውሻና ከዠንብ እየተጋፉ ከቁሻሻ መጣያ የእለት ጉርሳቸውን ሲቃርሙ በዓለም ቴሌቪዥኖች ለተተከለብን ኢፍትሃዊ አገዛዝ በኢግዚቢትነት ሲቀርቡ እያየን ስንሸማቀቅ ነው።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምና ክብር እናስቀድማለን ብለው የትነሱት የህዋት መሪዎችና አባላት ዛሬም ለቀጠለው ለዚህ አሳፋሪ ሁኔታ ዋናው ተጠያቂ የራሳቸው ጸረ ህዝብ አገዛዝ መሆኑን ተገንዝበው ለህዝባችን የተሻለ ቀን ለማምጣት፣ ዴሞክራሲና ሃቀኛ ብሄራዊ ውይይትን ለማራመድ በሚደረገው ትግል መተባበር ይኖርባቸዋል። ይህንን ካላደረጉ ስለ ብሄራዊ ጥቅም ማውራትና መሪዎች አጥቶ ገዥዎች ለዘመናት እየተፈራረቁ ላንገላቱት ህዝብ ቁመናል ማለቱ የማንም ሃቀኛ ዜጋ ህሊና የማይቀበለው መራራ ፌዝ ነው። እነዚህ ዜጎች ይህንን ሃቅ ተቀብለው ለዚህ እስካልታገሉ ድረስ የሃገር ጥቅም የሚለው መፈክራቸውን ከተራ የስልጣን ሽኩቻ፣ ጊዜያዊና ጠባብ ቡድናዊ ጥቅምን በአዲስ ዘዴ ለማራመድ ከተጠነሰሰ ጸረ ህዝብ ሴራና ስብብ ለይተን አናየውም።

ሁለተኛ/ ለኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና መብት ሊረጋግጥ የሚችለው በራሱ በህዝቧ ትግልና በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎው ነው ብለው እስካመኑ ድረስ ይህ አዲስ ሁኔታ ከነበሩ ትግልና ዓላማ የሚያዘናጋ ምንም ይዘት የለውም፡፡ የዚህ ህዝብ የወደፊት እድል ራሱ በትግሉና በመስዋእትነቱ በሚፈጥረው አስተማማኝ መሠረት ላይ የሚገነባ እንጂ በአንድ ድርጅት ወይም ቡደን ውስጥ በሚቀያየር የሃይል ሚዛን ላይ የሚንጠለጠል ነገር መሆን የለበትም፡፡ በተለይ ዛሬ በህዝባችን አላስተማማኝ በሆኑ ኃይሎች ሊወናበድና የትግል ትጥቁን ለጊዜውም ቢሆን ሊፈታ ያሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ስለምንገኝ ነበሩ የዴሞክራሲ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግላችን እጥፍ ድርብ ጉልበትና ጥራት ይዞ መንቀሳቀስ አለበት እንጂ ተዘናግቶ ማዘናጋት የለበትም፡፡

የፖልቲካ ትግላችን የወያኔን ጸረ ዴሞክራሲያዊነት ከማጋለጥ አልፎ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ያነገበ ትግል መሆን አለበት፡፡ አማራጫችን ደግሞ ሁሉም በየፊናው እያራገበ ህዝብን ግራ የሚያጋባበት የጨረባ ተዝካር አማራጭ መሆን የለበትም፡፡ በአነስተኛና በጋራ አማራጮች ላይ የጋራ ትግል የማካሄዱ ጉዳይ የመላው ህዝባችን ጥያቄ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡

በመሆኑም መሰሶን ለሁገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎችና በተለየም ደግሞ ለፓሪሱ ጉባኤ ጠንሳሽ ደርጅቶች በዚያ ጉባኤ መንፈስ እንደገና ተገናኝተውና በወንድማማችነትና በመከባበር መንፈስ ተወያይተው በጋራ በነደፉት ሰነድ አማካኝነት ፩ኛ/ ለነጻ ምርጫ 2ኛ/ ዴሞክራሲያዊ ህገመንግሥትን 3ኛ/ የብሄሮች ጉዳይና የኢትዮጲያን አንድነትን ጉዳይ 4ኛ/ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን 5ኛ/ በውያኔ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ የተነሳ ህዝቦችንን በመበከል ላይ ያለውን የብሄር ጥላቻ መርዝ በጋራ መዋጋትን አስመልክተን በዚያን ጊዜ የተስማማንባቸውን አቋሞች እንደገና በማደስ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት እንደገና በአዲስ መንፈስ በጋራ እንደንቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ሌሎች ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ዜጎችም በወቅቱ አድርገውት እንደነበረው በያሉበት በተለያዩ ኮሚቴዎችና ስብሰቦች አማካኝነት ለዚህ ሃሳብ ድጋፍ በመስጠት መንቀሳቀስ እንዲጀምሩ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

ሶስትኛ/ ለመላ የኢትዮጵያ ህዝብ፡ አገራችን ለምትገኝበት ከፍተኛ ቀውስ የተዳረገችው፣ ሌላው ቅርቶ ከቀሩት የአፍሪቃ አገሮች ተለይታ የችግር፣ የራሃብ፣ የጉስቁልና፣ የግፍና የደህነት ቋት የሆነቺው ለህዝብ ያልቆሙ፣ የህዝበን የልብ ትርታ የማይከተሉ፣ በህዝብ ፊት ምንም ተጠያቂነት የማይ ሰማቸው ገዢዎች እየተፈራረቁባት በመንገላታቷ ብቻ ነው፡፡ ገዥዎቻችን በእንደዚህ ዓይነት ግፈኛ ሥርዓት እጅ ተወርች አውተብትበው አስረውን አንዳንዴ " ለሃገር ብሄራዊ ጥቅምና ክብር ቆመናልና እቀፈን ደግፈን " ሲሉ ቀደም ሲልም በፊውዳሉና በደርግም ዘመን አይተነዋል፡፡ በዚህ መልክ ሰልፍ ባዘዙን ቁጥር የምንሰጠው ድጋፍ የዚችን አገር እድል ከጥቂቶች መዳፍ ፈልቅቀን እውጥተን ሚሊዮኖች እጅ ለማስገባት ከሚደረገው የደሞክራሲ ትግል ፈጽሞ መለየት የለበትም፡፡ በምንም ሰበብና ምክንያት ይሁን ለሃገር ጥቅምና ክብር የሚደረገው ትግል ከዴሞክራሲው ትግል ከተነጠለ ሃገር ጥቅም፣ ክብርና ሰላም፣አንድነትና ብልጽግና ለማረጋገጥ እንደማይቻል የፊውዳሉንና የደርጉ ዘመን ጭፍን ድጋፎች አስተምረውን አልፈዋል፡፡ ስለሆነም ይህ አዲሱ ምእራፍ አዎንታዊ ቀጣይነት የሚኖረው የወያኔ ኢህአዴግ መሪዎችም ካለፈው ተመክሮ ትምህርት ቀስመው ህዝቡ እድሉን እጁ ለማስገባት በሚያደርገው የዴሞክራሲ ትገል ሲተባበሩ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነና አሁንም የኢትዮጵያን

ህዝቦች መብት ማፈናቸውን ከቀጠሉ ከጠባብ አስተሳሰብ ያልተላቀቁ ፖለቲከኞች ናቸውና ህዝቡ በተገናው አጋጣሚ ሁሉ ከእንግዲህ የኢትዮጵያን ክብርና ጥቅም የሚያስጠብቁን ጉዳይ ከዴሞ ክራሲው ተጋድሎ ነጥሎ የሚያይበት ዘመን ያልቀ ያከትመ እንደሆነ እያስተጋባ ትግሉን ከዚ ህም አንጻር እንዲያፋፍም ጥሪ እናደርጋለን።

አራተኛ/ ለሚመለከትው ሁሉ። ይህ ግጭት በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች መካከል የሚካሄድ ግጭት አይደለም። አንዳንድ ክፍሎች ይህ መሰረታዊ ሃቅ ተረስቶ የህዝባችን የሃገር ፍቅር ስሜት ባልሆነ አግጣጫ እንድሄድና በነኢሳያስ አፈወርቂ ወታደራዊ አገዛዝ ታፍኖ ባልተመቸው የኤር ትራ ህዝብ ጥላቻ እንዲመነዝር ላይ ታች እንደሚሉ ግልጽ ነው። እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ የኢት ዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ታሪካዊ ትስስርና ወንድማማችነት ከሃላፊ አጥፊዎቹ ከነኢሳያስ አፈውርቂ እብሪት ምክንያት ነጥፎ ያለቀለት የሚያስመስል፣ አርቆ አስትዋይነት የጎደለው፣ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ከፖለቲካው አንጻር ሲታይ በአንድ በኩል የህዝባችንን ጉልብትና ትኩረት ከዋናው የትግል አግጣጫ ፈር የሚያስት፣ በሌላ በኩል የሻቢያን መሪዎች መሰሪ ስሌት የሚያግዝ በመሆኑ ወደ ህዝብ ጥላቻ የሚያመራን ማንኛውንም ቅስቀሳ ሆነ ድርጊት ሁሉም በአንድ ድምጽ እንዲያውግዘው ጥሪ እናቀርባለን።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ

እሁድ ግንቦት 9 ቀን 1990